# ጥናት አንድ ገላትያ 1፡1-10 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የደብዳቤው ጸሐፊ ገና ደብዳቤውን ሲጀምር በቁ1 ላይ እንደሚነግረን በጳውሎስ እንደሆነ ነው የምናየው። ጳውሎስ በዚህ ሥፍራ ከእርሱ ጋራ የነበሩትን ወንድሞች የጠቀሰበት ምክንያት ደብዳቤውን በመጻፍ እነርሱም ተባብረውኛል ወይም ደግሞ የእነርሱም እጅ አለበት ለማለት አይደለም፤ ነገር ግን ለገላትያ ሰዎች ሰላምታ የሚያቀርበው እርሱ ብቻ እንዳልሆነና ከእርሱ ጋራ የነበሩት ወገኖች ሁሉ ሰላምታቸውን እንደሚያቀርቡላቸው ለመናገር ነው።
2. ጳውሎስን በገላትያ መልዕክት ውስጥ ስንመለከተው ከበድና ጠንከር ባለ መንገድ የሚያስተላልፋቸው ብዙ መልዕክቶች ስላሉ አስቀድሞ የመልዕክተኛውን ማንነት ወይም የመልዕክት አምጭው ሥልጣን ሊረጋገጥ ስለሚገባ ይመስለኛል። ጳውሎስ የእግዚአብሄር መልዕክተኛ መሆኑን ብቻ ያበሰረ ሳይሆን፤ ከዚያው ጋራም አያይዞ የሰው መልዕክት ይዞ ወይም የሰው መልዕክተኛ ሆኖ እንዳልመጣም ነው የሚነግራቸው።
3. በቁ4 ላይ “እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ” በማለት የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በዘፈቀደ የሆነ ነገር ወይም ደግሞ በሰዎች አቅምና ጉልበት የሆነ ነገር ሳይሆን እግዚአብሄር አብ ራሱ ያቀደውና እንደ ፈቃዱ የተከናወነ ነገር መሆኑን ነው የምናየው። ስለ ኢየሱስ ሞት የተለየ ነገር የሚነግረን ነገር ቢኖር፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በፈቃዱ አሳልፎ እንደሰጠ እንጂ ሰውም ሆነ ሰይጣን አሸንፎ እንዳልወሰደበት ያረጋግጥልናል።
4. ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለእኛ ስለሰጠበት ምክንያት ከዚህ ክፍል መረዳት የምንችለው፤ “ከዚህ ክፉ ዓለም ያድነን ዘንድ” በማለት ነው የሚነግረን። ከዚህ ክፉ ዓለም እንደሚያድነን ሲነግረን፤ ከዚህ ዓለም ያወጣናል ሳይሆን በአንድ መልኩ ይህ ክፉ ዓለም በእኛ ላይ ሃይል እንዳይኖረው በማድረግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ልጆቹ በድል ሊመላለሱ የሚችሉበትን የመንፈስ ቅዱስን ሃይል በውስጣቸው ያኖራል ማለት ነው።
5. ጳውሎስ ምንም እንኳን በሕይወቱ ብዙ ነገሮችን ያየ ሰው ቢሆንም የእነዚህ ሰዎች ነገር ያስደነቀው ምክንያት፤ መጠራታቸውና እንዲኖሩ የሚጠበቅባቸው በጸጋ ሆኖ ሳለ ተመልሰው ወደ ግርዘትና ወደ ህግ መሄዳቸው በጭራሽ ሊዋጥለት ያልቻለ ነገር ነበረ። አዲስ የተቀበሉት ትምህርት ቀድሞ ጳውሎስ ካስተማራቸው የጸጋ ወንጌል ጋራ በምንም መልኩ የማይጣጣምና የማይዛመድ መሆኑ የተለየ ወንጌል የሚለውን ስያሜ አሰገኝቶለታል።
6. በቁ6 ላይ የተቀበሉትን የሃሰት ትምህርት የተለየ ወንጌል ብሎ መጥራቱ ከእውነተኛው ወንጌል የተለየ መሆኑን ለማሳየት ሲል እንጂ ጳውሎስ ከሰበከላቸው የክርስቶስ ወንጌል ሌላ የተለየ ወንጌል አለ ማለት አይደለም፤ ወንጌል ማለት የምሥራች ስለሆነ ሌላ ለሰው ልጆች ሁሉ የሚሆን የምስራች ከክርስቶስ ወንጌል ሌላ አይኖርም። እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች እያደረጉ ያሉት ሁለት ነገሮች አንደኛው የገላትያን አማኞች ማደናገር ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የወንጌሉን መልዕክት ማጣመም ናቸው።
7. በዚህ ቦታ ላይ “እኛ” የሚለውን ቃል የተጠቀመው በቁ1 ላይ አብረውኝ ያሉት ወንድሞች በማለት የተናገራቸውን ሰዎች ሊሆን ይችላል፤ ወይንም ደግሞ ምናልባትም የወንጌልን ሃላፊነት ከክርስቶስ የተቀበሉትን አሥራ ሁለቱን የጌታ ሐዋርያት ማለቱ ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ።
8. እንደ እኔ አመለካከት ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱንም ሳያስቀር፣ የሰማይ መላዕክትንም በመጨመር የዚህ ዓይነት የፍርድ ቃል መናገር የደፈረበት ምክንያት፤ የክርስቶስ ወንጌል አንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተሰጠ እውነት እንጂ በተፈለገ ጊዜ ማንኛውም ፍጥረት ሊቀያይረው የማይችለው ነገር መሆኑ በማያወላዳ መንገድ ማረጋገጥ ስለፈለገ ነው።

# ጥናት ሁለት ገላትያ 1፡11-24 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህ ጳውሎስ እየሰበከ የሚገኘው ወንጌል በመጀመሪያ ደረጃ ሰው ሰራሽ የሆነ ነገር እንዳልሆነ ይናገራል፤ በመቀጠል ከሰው የተቀበለው እንዳልሆነ፤ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ከማንም ሰው አልተማርኩትም ሲለን፤ በአራተኛነት የሚናገረው በመገለጥ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለው መሆኑን ነው። በቁ12 ላይ "ከኢየሱስ ክርስቶስ ተቀበልሁት" የሚለው አነጋገሩ እርሱም ራሱ እንኳን ቢሆን የወንጌል ምንጭ እንዳልሆነና በመገለጥ የተቀበለው ነገር እንደሆነ ይነግረናል።
2. በገላትያ 1፡ ቁጥር11 እና ቁ12 ላይ የእግዚአብሄር ቃል ምንጩ ምድራዊ ማለትም ሰው ሰራሽ እንዳልሆነ ጳውሎስ በተለያየ መንገድ የገለጸውን፤ ጳውሎስ ደግሞ "ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም" በማለት ያንኑ ሃሳብ በሌላ መንገድ ያረጋግጥልናል።
3. እነዚህ ቁጥሮች በሶስት መንገድ የጳውሎስን የክርስትና ጉዞ የሚከፍሉት፤ የመጀመሪያው ክርስቶስን ከማግኘቱ በፊት የነበረው ሕይወት ሲሆን፣ ሁለተኛው ክርስቶስን ስለተገናኘበት ወቅት፣ ሶስተኛው ደግሞ ክርስቶስን ከተገናኘ በኋላ የነበረውን ሕይወት የሚናገር ነው።
4. ጳውሎስ ክርስቶስን ከመገናኘቱ በፊት፤ በአይሁድ ሃይማኖት የሚኖር ሰው ነበረ፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በእጅጉ የሚያሳድድ ሰው ነበረ፣ ቤተ ክርስትያንን ለማጥፋት የሚጥር ሰው ነበረ፣ በዚያን ዘመን ከነበሩት ከብዙዎቹ አይሁዶች ይልቅ የአይሁድን ሃይማኖት አጥብቆ ይከተል ነበር፤ ስለ አባቶች ወግም እጅግ የሚቀና ሰው ነበረ። በሮሜ 10፡2 ላይ "ለእግዚአብሔር ቀናተኞች እንደሆኑ ስለ እነርሱ መመስከር እችላለሁና፤ ቅናታቸው ግን ከዕውቀት የተነሣ አይደለም" በማለት እንደተናገረው፤ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥም እንዳየነው እርሱም የጌታ ነገር እስከሚበራለት ድረስ ለእግዚአብሄር በነበረው ቅናት የማይገባውን ሁሉ እንዳደረገ አሳይቶናል።
5. ቤተ ክርስትያን ሰዎች ስለፈለጉ ወይም ደግሞ በሰዎች ውሳኔ የተገኘች ሳትሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የመሰረታት በመሆኗ፤ ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ ቤተ ክርስትያን ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ምንም ዓይነት የገሃነም ሃይል ተነስቶ ሊያጠፋት ቢሞክርም እንኳን ሊያጠፋት የማይችል ተቋም እንደሆነች እናያለን፤ ለዚህም ነው እንደ ጳውሎስ ያሉ ብዙዎች ያላቸውን ሁሉ ሃይላቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ጊዜያቸውን ሁሉ ቢያጠፉም እነርሱ ይጠፋሉ እንጂ ቤተ ክርስትያንን ማጥፋት አይችሉም።
6. እግዚአብሄር በሕይወቱ እንዳደረገ በሙሉ ልብ የተቀበላቸው ሶስቱ ነገሮች፡- አንደኛው ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ የለየው እንደሆነ፣ ሁለተኛው እግዚአብሄር በጸጋው የጠራው መሆኑና፤ ሶስተኛው ደግሞ ስለ እርሱ በአህዛብ መሃል እንዲሰብክ መፈለጉ ናቸው። ጥሪው ከእግዚአብሄር በደረሰው ጊዜ ከማንም ሥጋ ለባሽ ጋር አልተማከረም፤ ከእርሱ በፊት ሐዋርያት ወደ ሆኑትም ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣም፤ ነገር ግን ወዲያው ወደ ዐረብ አገር እንደሄደና ቀጥሎም ወደ ደማስቆ እንደተመለሰ እናነባለን።
7. በዚህ እኛ ባለንበት ዘመን የጳውሎስ ዓይነት ከፍተኛ ሥፍራ የነበረውና የእርሱን ያህል የታወቀ ሰው ጌታን ቢቀበል እንኳንስ በአማኞች ሳይታወቅ ሶስት ዓመት መክረም ይቅርና ገና ተቀብያለሁ ብሎ ሳይጨርስ ማን ወደ ጌታ እንዳመጣው፣ የማን ቤተ ክርስትያን አባል እንደሆነና የሚፈልገውን ዓይነት አገልግሎት ተጠይቆ እንደሚሰጠው አልጠራጠርም። ከዚህ ልንማር የሚገባ የሚመስለኝ ሰዎች ገና ደህንነታቸውን ሳያጣጥሙ ዘሎ መድረክ ላይ ማውጣት ለትዕቢትና ለውድቀት ማጋለጥ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ነው።

<u>ጥናት ሶስት ገላትያ 2፡1-10 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ገላትያ 2፡1ድን ብቻ በመመልከት በእነዚህ ሁለት የጳውሎስ ጉዞዎች መሃል እንዳለ የሚታየኝ ልዩነት፤ በመጀመሪያ ጉዞው ማንም ከእርሱ ጋራ እንደሄደ የሚናገረው ነገር ስለሌለ ለብቻው እንደሄደ እገምታለሁ፤ በሁለተኛው ጉዞው ግን በርናባስንና ቲቶን ከእርሱ ጋራ መውሰዱ ከመጀመሪያው ይለየዋል ብዬ አምናለሁ። የመጀመሪያ ጉዞው ጴጥሮስን ለማግኘት ሲሆን፣ ሁለተኛው ጉዞ ግን እግዚአብሄር የነገረው ወይም የገለጠለት ነገር ስለነበረ በዚያ ምክንያት ነው የሄደው።
2. ኢየሩሳሌም እንደደረሰ ያደረገው ነገር ቢኖር በአሕዛብ መካከል እየሰበከ ያለው ወንጌል ምን እንደሆነ መግለጥ ሲሆን፤ ይሁንንም ያደረገበትን ምክንያት ሲናገር፤ ልፋቱና ጥረቱ በከንቱ እንዳይሆን በመሥጋትና ይህንንም ሲያደርግ ሕዝብን ሁሉ ሰብስቦ ሳይሆን ዋነኞች ብሎ ለሚያምናቸው ሰዎች በግል በመሰብሰብ ነበረ።
3. ከዚህ ከጳውሎስ አነጋገር ከሃዋርያቱ ጋራ ስለተደረገው ውይይት የሚጠቁመን ነገር አለ ብዬ አምናለሁ፤ ይኸውም በዚህ ክፍል ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በመልዕክቱ ውስጥ የሚታየውን የአህዛብን የመገረዝና ያለመገረዝ ነገር የተወያዩበት በመሆኑ ይመስለኛል በቁ3 ላይ የቲቶን ግርዘት ነገር በማንሳት የተናገረው። እነዚህ ሰዎች ሃሳባቸውን ለመፈጸም የሚመጡበት መንገድ ግልጽና ፊት ለፊት ሳይሆን ሾልከው በመግባት ነው፤ ዓላማቸውና ግባቸውም አማኞች በክርስቶስ ያገኙትን ነጻነት እንደገና ወደ ባርነት ቀንበር መመለስ ነው።
4. ሐዋርያው በቁ5 ላይ "የወንጌል እውነት ከእናንተ ጋር ጸንቶ እንዲኖር ነው" በማለት እንደሚናገረው ሁሉ ማንኛውም የክርስቶስ ኢየሱስን ወንጌል ለሰዎች የሚያበስር ሰው ሁሉ ያ የተዘራው ዘር በሰዎቹ ሕይወት ውስጥ ጸንቶ እንዲኖር ለማድረግ መጣር ያስፈልጋል። ከዚህ ቁጥር ላይ እንደምንረዳው ጳውሎስ እንዲሁ እግረ መንገዱ ያደርገው የነበረ ነገር ሳይሆን "ለእነዚህ ሰዎች ለአንድ አፍታ እንኳ አልተገዛንላቸውም" በማለት ባለው ሃይሉ ሁሉ የሚያደርገው ነገር እንደነበረ እንረዳለን።
5. በርግጥም ይህ አይነቱ አነጋገር ትዕቢት ያለበትና ንቀት የተሞላው መስሎ ሊታይ ይችላል፤ ሆኖም ሐዋርያው ጳውሎስ በዚያ ዓይነት መንፈስ እንዳልተናገረው ማወቅ የምንችለው ቁ2 "ዋነኞች ለሚመስሉት ብቻ በግል ይህን አስታወቅኋቸው" በማለት ለእነዚህ ሰዎች የነበረውን አክብሮት አስቀድሞ ግልጽ በማድረጉ ነው። ከተቀበለው መልዕክት አንጻር ግን እግዚአብሄር ለእርሱ ከሌሎቹ ሐዋርያት  ያነሰና ዝቅ ያለ መልዕክት እንዳልሰጠውና የእርሱ ሐዋርያነትም ከእነርሱ ዝቅ ያለ እንደሆነ አድርገው በመናገር ሥልጣኑን ለሚንቁት መልስ የሰጠበት መንገድ እንደሆነ አምናለሁ።
6. እነዚህ ሁለት ሐዋርያቶች ምንም እንኳን ወንጌልን የመስበክ ጥሪ ቢኖራቸውም፤ በዚህ ቁጥር ላይ እንደሚነበበው የጴጥሮስ ጥሪ ወደ ተገረዙት ወይም ወደ አይሁድ ሲሆን፤ የጳውሎስ ጥሪ ደግሞ እንደሆነ የተነገረን ወዳልተገረዙት አህዛብ መሆኑን እናያለን። በቁ3 ላይ የተነገረውን እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አለማድላቱን በቁ8 ላይ የሚረጋገጠው፤ እግዚአብሄር በጳውሎስና በጴጥሮስ መሃል ሳይለይ ለሁለቱም የሰጣቸውን አገልግሎት እንዲወጡ ብቃት በመስጠትና በማስቻሉ ነው።
7. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እንደምናየው "ያዕቆብ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስም የተሰጠኝን ጸጋ ባስተዋሉ ጊዜ" በማለት ለጳውሎስና ለበርናባስ የትብብር ቀኝ እጃቸውን የሰጧቸው ዋነኛ ምክንያት የተሰጠውን ጸጋ ማየት ስለቻሉ እንደሆነ እንመለከታለን።
8. ጳውሎስ የተቀበለው ወንጌል ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ የገለጠለት እንደሆነ በግልጽ የተናገረውን የወንጌል መልዕክት እንደሆነ እያወቀ፤  ከሌሎቹም ሐዋርያት መልዕክት ጋራ ለማነጻጸርና የእነርሱንም ሃሳብ ለመስማት ክፍት መሆኑ የዚህን ሰው ትህትና ብቻ ሳይሆን በእርሱ የሰራውና እግዚአብሄር በሌሎችም ውስጥ ሊሰራ እንደሚችል የተቀበለ መሆኑ ግልጽ ነው፤ ስለዚም እኛ ከጳውሎስ ድርጊት መማር የምንችለው ነገር ቢኖር፤ እኛ ብቻ ትክክለኛና አዋቂ እንደሆንን አድርጎ ከመቁጠር ትዕቢት ራሳችንን ልንጠብቅ ያስተምረናል።

# ጥናት አራት ገላትያ 2፡11-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ አንጾኪያ ቤተ ክርስትያን መመምጣቱ አስቀድሞ የነበረበትን ሥፍራ ለማወቅ ባለፈው ሳምንት የተጠናውን ክፍል ገላትያ 2፡1-10ን ያስፈልጋል። ጳውሎስ ከአስራ አራት ዓመታት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ የሚሰብከውን ወንጌል ሰብስቦ ካናገራቸው ሰዎች መሃል ጲጥሮስ እንደነበረበት ቁ9 ስለሚነግረን ጲጥሮስ የመጣው ከኢየሩሳሌም ነው ማለት በእርግጠኛነት መናገር እንችላለን።
2. እንደ እኔ አመለካከት በዚህ ክፍል ውስጥ ጲጥሮስ ያሳየው የግብዝነት ድርጊት ሐዋርያው ጳውሎስ ሌሎች እያዩና እየሰሙ ጠንከር ባለ መልኩ መገሰጽ የነበረበት ምክንያት፤ ድርጊቱ በእርሱ ላይ ያቆመ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው የነበሩትን አማኞችም ጭምር ወደ ስህተት መንገድ የጨመረ ብቻ ሳይሆን ከጳውሎስ ጋራም በወንጌል አገልግሎት የተሰማራውም በርናባስም እንኳን ሳይቀር ጲጥሮስ በከፈተው የስህተት በር ለመግባት እግሩን እስከሚያነሳ ድረስ በማድረሱ ከግል ያለፈ ተግሳጽ አስፈላጊ ነበረ እላለሁ።
3. በቁ13 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ በርናባስ የዚያን ዓይነት ሃሳብ መሰንዘሩ ለእኔ የሚነግረኝ እውነት ቢኖር፤ በርናባስ እንደዚህ በቀላሉ ከወንጌል እውነት ገሸሽ የማይል፣ በአቋሙ ጽኑ የሆነና ጳውሎስ የሚተማመንበት ዓይነት ሰው እንደነበረ፤ ሆኖም በዚያ ሥፍራ የነበረው ሁኔታ ምን ያህል ከባድና ለጠንካሮች እንኳን አስቸጋሪ እንደነበረ ነው ከአነጋገሩ የምረዳው።
4. ጲጥሮስ ያደረገውን ዓይነት ድርጊት ሌሎችም ሰዎች እንዳደረጉ በቁ14 ላይ "ተግባራቸው" ከሚለው ቃል የምንረዳ ቢሆንም እንኳን፤ ጲጥሮስ እንደ ሃዋርያና እንደ ቤተ ክርስትያን መሪ ከሌሎቹ ሚዛን ከፍ ብሎ ሊገኝና ለሌሎቹ መልካም ምሳሌ እንዲሆን ስለሚጠበቅብት ነው ብዬ አምናለሁ። "ተግባራቸው እንደ ወንጌል እውነት አለመሆኑን በተረዳሁ ጊዜ" የሚለው አነጋገር የሚያስተምሩት የወንጌል እውነት ከሚኖሩት ኑሮ ወይም ደግሞ ከተግባራቸው ጋራ አለመጣጣሙ ችግር እንደፈጠረ ነው በዚህ ክፍል ውስጥ የምናየው።
5. ጳውሎስ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሰው ምንም ዓይነት ጥያቄ ሊያነሳ በማይችልበትና ግልጽ ባለ መንገድ እንዲረዱት የፈለገው አንድ እውነት ቢኖር፤ ሰው ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ፣ ሕግን በመጠበቅ እንደማይጸድቅ፤ እንዲሁም ደግሞ አይሁድም ቢሆኑ ከዚህ የተለየ ሌላ የጽድቅ መንገድ እንደሌላቸውና ለመጽደቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስፈልጋቸዋል የሚለው እውነት ነው። በዚያ ቁጥር ላይ "እኛ" እያለ የሚናገረው እርሱንና ሌሎቹን አይሁዶች ከአህዛብ ጋራ እያነጻጸረ የተናገረበት ሁኔታ ነው።
6. ሐዋርያው ጳውሎስ በእግዚአብሄር ፊት ጻድቅ ሆኖ ለመገኘት በክርስቶስ ባመነ ጊዜ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት እርሱም ለሕግ እንደሞተ፣ ወይም ከክርስቶስ ጋራ እንደተሰቀለ ሲናገር፤ ለዚህ ለመሆኑ ምክንያት አድርጎ የሚነግረን በቁ19 ላይ የምናየው "ለእግዚአብሔር እኖር ዘንድ" የሚለው ሃሳብ ነው። ለእኔ በሁለቱ ሃሳቦች መሃል ቅራኔ አላይም፤ ምክንያቱም "ከእንግዲህ እኔ አልኖርም" የሚለው እንደ ቀድሞው በራሴ ሃይልና ጉልበት ሕግን ለመፈጸም አልፍጨረጨርም ሲሆን፤ "አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ" የሚለው ደግሞ በውስጡ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ሃይል የሚኖረውን ሃሳብ የሚናገር ነው።
7. በደንብ ራሱን ሊያሳምን የሚችልበት ምክንያት ለራሱ ሰጥቶ ዝም ማለት ይችል ነበረ ብዬ አምናለሁ፤ ለዚህም ምክንያት ሊሆነው የሚችለው በመጀመሪያ ደረጃ ጲጥሮስ ከእርሱ በፊት ጌታን የሚያውቅ ሰው ብቻ ሳይሆን ከእርሱ በፊት ሐዋርያ የነበረ ሰው መሆኑ አንዱ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ይኸ ሁሉ ሰው አንዳች ነገር ሳይናገር፤ እንዲያውም አስቀድሞ ጌታን የሚያውቀው በርናባስም ጭምር ዝምታን ከመረጡ እኔ ከወንድሜ ጋራ ምን አጋጨኝ አርፌ በሰላም ጌታ የሰጠኝን አገልግሎት አላገለግልም ወይ ማለት ይችል ነበረ።

# ጥናት አምስት ገላትያ 3፡1-14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በእነዚህ አምስት ቁጥሮች ላይ ብቻ ሐዋርያው ጳውሎስ የገላትያን አማኞች የጠየቃቸው ስድስት ጥያቄዎች እንደነበሩ መመልከት እንችላለን። ሐዋርያው በገላትያ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ስለተከሰተው ሁኔታ የተሰማውን ስሜት ብዙ ርቆ ማንበብ እንኳን አያስፈልግም፤ ምክንያቱም ቁ1 ላይ የምናየው ሰዎቹን ለመጥራት የተጠቀመበት “እናንተ የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ” የሚለው አነጋገሩ ምን ያህል ውስጡ እንደበገነ የሚያሳየን ነው።
2. የገላትያን አማኞች ከእውነተኛ ወንጌል በተጨማሪ ሌላ ነገር ማድረግ ወይም መፈጸም እንደሚኖርባቸው ለማድረግ ሃሰተኛ አስተማሪዎቹ የተጠቀሙበትን መንገድ ለመጥቀስ ጳውሎስ በቁ1 ላይ የተጠቀመበት ቃል “መተት” የሚለው ነው። የገላትያ ሰዎች ምንም እንኳን ቀስ በቀስ ወደ ሥህተት ጎዳና እያቀኑ እንደሆነ ቢያውቅም፤ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄር መንፈስ በውስጣቸው እንዳለና የእግዚአብሄር ልጆች እንደሆኑ ተቀብሏል።
3. እነዚህ ሰዎች የክርስትናን ህይወት የጀመሩት ወይም መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት የተሰበከላቸውን ወንጌል በመቀበል ሲሆን አሁን ግን እያደረጉ ያሉት ሕግን ወደ ሕግ መጠበቅ እንዳዘነበሉ (ቁ2)፤ ወይም ደግሞ በሌላ አነጋገር ሲናገር፤ ጅማሬአቸው በመንፈስ እንደሆነ ለመጨረስ የሚሞክሩት ግን በሥጋ እንደሆነ (ቁ3) ነው የሚናገረው።
4. አማኞችን ሁሉ ከአብርሃም ጋራ አንድ የሚያደርገን ነገር ቢኖር በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ክፍሎች እንደምናገኘው አብርሃም ጸደቀ የሚለን እግዚአብሄርን በማመኑ እንደነበረ ሁሉ፤ በየትኛውም ዘመን ያሉ እምነታቸውን በክርስቶስ የመስቀል ሥራ ያደረጉ ሁሉ አብርሃም በእምነት እንደጸደቀ እነርሱም በእምነት ጸድቀዋልና ይህ አንድ ያደርጋቸዋል።
5. በገላ 3፡6-9 ላይ ጳውሎስ የሚናገረው የአብርሃም ልጅ ለመሆን የሚያስፈልገው ነገር አብርሃም እግዚአብሄርን በማመን እንደጸደቀ  ክርስቶስ የሰራውን የደህንነት ሥራ በማመን መጽደቅ እንደሆነ ሲናገር፤ ክርስቶስም በዮሐ ወንጌል 8፡39 ላይ አይሁዳዊያኑ ስለ አብርሃም ልጅነት የነበራቸውን የተሳሳተ አመለካከት በማረም የአብርሃም ልጅ ለመሆን አብርሃም የሰራውን ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ያም ደግሞ በእምነት እግዚአብሄር የላከውን ክርስቶስ ማመን እንደሆነ ማስረዳቱ ሁለቱን ጥቅሶች ያመሳስላቸዋል።
6. ቁ8 ላይ እንደምናነበው የወንጌልን መልዕክት ከሁሉ አስቀድሞ የሰማው ሰው አብርሃም እንደነበረ እንመለከታለን። በዚያን ጊዜ ለአብርሃም የወንጌሉን መልዕክት ያበሰረው ወንጌላዊም እግዚአብሄር ራሱ እንደነበረ ከዚህ ቁጥር መረዳት ይቻላል። በዚህ ቁጥር ላይ ስንመለከት በረከት የሚለው ሃሳብ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ከወንጌል ማለትም በእምነት ከሚገኘው ጽድቅ ጋራ አዛምዶት ነው የምንመለከተው።
7. ይህ ክፍል የሚነግረን ሕግን ሁሉ አንዲቷም እንኳን ዝንፍ ሳትል መጠበቅ የሚችል ሰው ቢገኝ በሕግ እንደማይድን ሳይሆን የሚነግረን ሕግን ሁሉ በአንዷም እንኳን ሳይስት ሕግን በሙሉ ለመጠበቅ የሚችል ሰው ሊገኝ ስለማይችል ነው በሕግ ሊዳን የማይቻለው።
8. አዎን በሚገባ ተፈጻሚነት አግኝቷል ብዬ አምናለሁ፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ እርግማን ሆኖ የሞተው ሞት በቀደሙት ዘመናት የነበሩት ብቻ ሳይሆኑ ዛሬም በአለማችን ዙሪያ የሚገኙት አማኞች ሁሉ በአብዛኛው አህዛብ እንጂ አይሁዳውያን አለመሆናቸው የዚህ እውነት ማረጋገጫ ሆኖ ይታያል።

# ጥናት ስድስት ገላትያ 3፡15-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. “በዚህ ጉዳይ” ሲል ጳውሎስ ሊያያይዝ ያሰበው ሃሳብ ከላይ በመጀመሪያዎቹ 14 ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ለአብርሃም አህዛብን በእርሱ በኩል እንደሚባርክ የገባውን የተስፋ ቃል በማስመልከት ክዚያ ሃሳብ ጋራ እንደተያያዘ ነው የማየው፤ በተጨማሪም ቁ16 ላይም በመቀጠል መናገር የያዘው ያንኑ ሃሳብ አስመልክቶ ነው።
2. ከዚሁ ከቁ16 ላይ እንደምንረዳው “ለዘርህ” በሚለው ሃሳብ ላይ የተመሰረተው የእግዚአብሄር የተስፋ ቃል በአንድ ሰው ላይ ብቻ ያተኮረና ያም ደግሞ ክርስቶስ ኢየሱስ ሲሆን፤ “በዘሮችህ” የሚለው ሃሳብ ግን የብዙ ቁጥርን ስለሚያመለክት ይህ ነው የሚባልን ሰው ስለማያሳይ ግራ የሚያጋባ የተስፋ ቃል ይሆን ነበር። ከዚህም ለራሳችን መማር የምንችለው፤ ትንሽ የሚመስለን ነገር ያልታሰበ ውጤት ሊያስከትል ስለሚችል የእግዚአብሄርን ቃል በጥንቃቄ ልናጠናው እንደሚገባን እንማራለን።
3. በቁ17 ላይ “ከአራት መቶ ሠላሳ ዓመት በኋላ የተሰጠው ሕግ፣ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የጸናውን ኪዳን አፍርሶ የተስፋውን ቃል አይሽርም” በማለት ስለሚነግረን ለአብርሃም የተሰጠው የተስፋ ቃል ወይም ጸጋው (ቁ18) ከሕግ እንደሚቀድም መረዳት እንችላለን። እግዚአብሄር ለአብርሃም ርስትን ለማውረስ የተጠቀመበት መንገድ ጸጋ እንደነበረ የሚነግረን ጥቅስ ቁ18 ላይ የምናነበው ሃሳብ ነው።
4. ቁ19ኝን ስናነብ ጳውሎስ ራሱ ይህንኑ ጥያቄ ራሱ ጠይቆ መልስ ሲሰጠበት እናያለን። ሕግ የተሰጠው መተላለፍ እየበዛ ስለሄደ እግዚአብሄር ለአብርሃም የገባው የተስፋ ቃል እስከሚፈጸም ድረስ በጊዜአዊነት እንዲያገለግል እንደነበረ ይነግረናል። እግዚአብሄር ሕግን ሲሰጥ ሰዎች ሕግን በመጠበቅ ህይወት እንዲያገኙ በማሰብ እንዳልነበረ በቁ21 ላይ ይነግረናል።
5. ሰዎች ሁሉ ማለትም አንድ ሰው እንኳን ሳይቀር በሐጥያት ሥር ሆኖ መቆየቱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በማመን የሚገኘው ተስፋ ለተወሰኑት ብቻ ሳይሆን ሰዎችን ሁሉ የሚያጠቃልል የደህንነት መንገድ እንዲሆን ነው።
6. እምነት እስከሚገለጥበት ጊዜ ድረስ ሰዎች ሁሉ በህግ አማካኝነት እስረኞችና የተዘጋብን ነበርን፤ ሕግ እምነት እስኪመጣ ድረስ የእኛ ሞግዚታችን ነበረ፤ አሁን እምነት ስለተገለጠ ጠባቂ ወይም ሞግዚት አስፈላጊያችን አይደለም። ለእኔ የሚታዩኝ ሶስት እውነቶች፡ የመጀመሪያው የእግዚአብሄር ልጅነት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንደሆነ፤ ሁለተኛው እውነት ሁላችን የተጠመቅነው ከክርስቶስ ጋራ አንድ ለመሆን እንደሆነ (1ኛ ቆሮ 12፡13)፤ ሲሆን ሶስተኛው የሚታየኝ እውነት ደግሞ ከክርስቶስ ጋራ የተጠመቅን ሁላችን ደግሞ ክርስቶስን መልበሳችን ነው።
7. እነዚህ ሌሎችን ሰዎች የሚከፋፍሉና እስከ ሞት ድረስ ሊያዳርስ የሚያበቃ ልዩነትን የሚያደርጉት እንደ ዘር፣ ጎሳ፣ ቋንቋና ነገድ የመሳሰሉት ነገሮች ወደ አማኞች ሲመጡ፡ ኤፌ 2፡14 ላይ “ሁለቱን አንድ ያደረገ፣ የሚለያየውንም የጥል ግድግዳ ያፈረሰ ሰላማችን እርሱ ራሱ ነውና” በማለት እንደተነገረው የጥል ግድግዳ ሊሆኑ ያላቸው ነገሮች ሁሉ በክርስቶስ ሞት ስለፈረሱ መልሶ ግድግዳን መገንባት የመስቀሉ ሥራ ጠላት እንደ መሆን ስለሚቆጠር ሰላማችንን በክርስቶስ ይዘን መኖር ይገባናል ማለት ነው።

# ጥናት ሰባት ገላትያ 4፡1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ወራሹ ሕጻን ልጅ በመሆኑ ምክንያት ብቻ የአባቱን ርስት የመውረስ መብት ቢኖረውም እንኳን እድሜው ገና ለውርስ የሚያበቃው ባለመሆኑ ምክንያት የተወሰነው ቀን እስከሚደርስ ድረስ ውርሱን መቀበል ስለማይችል፤ የውርስ ሥልጣን የሌለው በቤቱ ውስጥ የሚኖረው ባሪያ ሕጻኑ ልጅ እድሜው እስከሚደርስ ድረስ ከእርሱ በምንም የተለየ እንዳልሆነ ነው የሚያስተምረን።
2. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አመጣጥ ሁኔታ የተናገራቸውና በቁ4 ላይ ሰፍረው የማያቸው ነገሮች፡ አንደኛው ኢየሱስ የመጣው ዘመኑ ሲደርስ እንደነበረ ይናገራል። ሁለተኛው ኢየሱስ ከሴት የተወለደ ነው፤ ሶስተኛው ደግሞ ከህግ በታች ሆኖ ነው የተወለደው። ቁ5 እንደሚነግረን ደግሞ ኢየሱስ ይህንን ሁሉ የሆነው እኛ ከህግ በታች የነበርነው የልጅነትን መብት እንድናገኝ ሲሆን፤ ቁ 6 ደግሞ ልጆች ስለሆንን መንፈሱ በእኛ ውስጥ እንዲኖር ሰጠን።
3. ሐዋርያው በዚህ ሥፍራ “ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም” ማለቱ እግዚአብሄርን ከአሁን በኋላ አታገለግልም ማለቱ አይደለም፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመጣና ከህግ ሞግዚትነት ነጻ ወጥተን ወራሾች ሆነናል። ስለዚህም ባሪያ ወራሽ ስላልሆነና እኛ ግን ልጆች በመሆናችን ወራሾች ስለሆንን ያንን እውነት ሊያስረዳን የተናገረው ንግግር እንደሆነ ነው የምረዳው።
4. እነዚህ ሰዎች ጌታን ከማወቃቸው በፊት አማልክት ላልሆኑ የተለያዩ ነገሮች ባርያዎች እንደነበሩ፤ አሁን ግን እውነተኛ አምላክ የሆነውን እግዚአብሄርን እንዳወቁት ወይም ደግሞ በእርሱ የታወቁ እንደሆኑ ነው የሚያስረዳቸው። የገላትያ ሰዎች ይህንን ያገኙትን አዲስ የሆነ በረከት ትልቅነት ለማሳየት ሲል የጠየቃቸው ሁለት ጥያቄዎች “ታዲያ እንደ ገና ወደ ደካማና ወደማይጠቅም ትምህርት እንዴት ትመለሳላችሁ? ዳግም በእርሱ በባርነት ለመጠመድ ትፈልጋላችሁን?” በማለት ወደ ልባቸው ሊመልሳቸው ሲሞክር ነው የምናየው።
5. ጳውሎስ በዚህ ቦታ “እነዚያ ሰዎች” በማለት የሚናገራቸው ሰዎች፤ የገላትያን አማኞች ከእውነተኛው የእግዚአብሄር አምልኮ አውጥተው በሕግና በሥርዓት የመጽደቅ ሕይወት ውስጥ ሊያስገቧቸው እየተሯሯጡ ያሉትን የሐሰት አስተማሪዎች ማለቱ ነው። ስለ እነዚህ ለእነርሱ ተቆርቋሪ መስለው ስለተነሱት የሃሰት አስተማሪዎች ጳውሎስ ሊያሳያቸው የሚሞክረው እውነት፤ ሰዎቹ አማኞቹን ከእነ ጳውሎስ የመለየትና ከእነርሱ ጋራ የሚቆሙ ለማድረግ እንጂ እነርሱን በምንም መንገድ የመጥቀም ሃሳብ እንደሌላቸው ሊያሳይ ነው እየሞከረ ያለው።
6. ጳውሎስ በኤፌሶን 4፡15 ላይ በቃል የተናገረውን እውነት በዚህ ክፍል ውስጥ በተግባር ተፈጻሚ ሲያደርገው ያየሁበት መንገድ ቢኖር፤ የገላትያን ሰዎች እንደሚወዳቸው በቁ19 ላይ ግልጽ አድርጎ የተናገረ ሲሆን፤ ለእነርሱ ያለውን ፍቅር የተጠቀመው ግን እውነትን ለመናገር እንደሆነ አያለሁ።
7. ሐዋርያው የዚህን ዓይነት አነጋገር ስሜታዊ የሆነ አነጋገር ሲናገር በውስጡ ይሰማው የነበረውን ስሜት ሳስብ እንደ እርጉዝ በጭንቅና በምጥ ውስጥ ያልፍ እንደነበረ ብዙ ሳንሄድ ከክፍሉ የምናነበው ነገር ይጠቁመናል። ይህንን ያህል የጭንቀት ነገር እንዲሰማው የመሆኑን ነገር ስናስብ ደግሞ፤ አንድ ሰው ለሌላ ሰው ይህንን ያህል ስሜት የሚሰማው ከሆነ ምን ያህል ለሰውየው ፍቅር እንዳለው ወይም ደግሞ የመውደዱን ጥልቀት የሚያስረዳ እንደሆነ ግልጽ ይመስለኛል።
8. “እውነቱን ስለ ነገርኋችሁ ጠላት ሆንሁባችሁን?” የሚለውን አነጋገር እኔ የምረዳው፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ቀደም ሲል ከገላትያ ሰዎች ጋራ የነበረው ሞቅ ያለ ግንኙነት ዛሬ መልኩን እንደለወጠ፤ ማለትም ከመልካም ወደ መጥፎ እንደሄደና ይህም የሆነበት ዋነኛውና ብቸኛ ምክንያት እርሱ ለእነርሱ ያለው ፍቅር ስለተለወጠ ወይም ደግሞ የተለየ ክፉ ነገር አድርጎ ሳይሆን የወንጌልን እውነት ፊት ለፊት ሳያመቻምች ሳስለነገራቸው ነው። እኛም ብንሆን ሰዎችን ከሰዎች ጋራ ያለንን መልካም ግንኙነት ለመጠበቅ ስንል እውነቱን ከመናገር ወደኋላ ማለት እንደሌለብን መቁረጥ ይኖርብናል።

# ጥናት ስምንት ገላትያ 4:21-31 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የጳውሎስ አድማጮች እንደሆኑ የምናያቸው ሰዎች በቁ21 ላይ “እናንት ከኦሪት ሕግ በታች ለመኖር የምትሹ” በማለት የሚናገራቸው ከህግ በታች የመኖር ፍላጎትና አዝማሚያ የነበራቸው ሰዎች ናቸው። የአብርሃምን ሕይወት በዚህ ሥፍራ ሕግን ለማስተማር ያንሳው እንጂ፤ መጽሐፍ ቅዱሳችን የአብርሃምን ስም ሲያነሳ የእምነት አባት በማለት አብዛኛውን ጊዜ ከእምነት ጋራ በተያያዘ መልኩ ነው ሲነሳ የምናገኘው።
2. በዚህ በታ ላይ ጳውሎስ እነዚህን ስለ ሕግ ለማስተማር የተጠቀመባቸውን ሁለት ሴቶች የሚጠራቸው ባሪያይቱና ነጻይቱ በማለት ነው ሲጠራቸው የምንመለከተው። በዚህ ሥፍራ ህግን አስመልክቶ ትምህርት የሚሰጣቸው ሰዎች ስለ እነዚህ ሁለት ሴቶ ማንነት ጠንቅቀው የሚያውቁ ስለሆነ መጠሪያ ስማቸውን መጥቀስ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም፤ ሆኖም እኛ እነዚህን ሴቶች የምናውቃቸው ባሪያይቱ አጋር ስትሆን፤ ጨዋይቱ ወይም ደግሞ ነጻይቱ እያለ የሚጠራት ሳራ ናቸው።
3. እነዚህ ሁለት ልጆች ምንም እንኳን አንድ አባት አብርሃም እንደወለዳቸው ቢታወቅም አወላለዳቸው በጭራሽ አንደኛው ከሌላኛው የማይገናኝ ዓይነት ነው። የባሪያይቱ ልጅ እንደ ሥጋ ፈቃድ የተወለደ ሲሆን የነጻይቱ ልጅ ግን እንደ ተስፋ ቃል የተወለደ መሆኑን ጸሐፊው ግልጽ ያደርግልናል። ጸሐፊው እነዚህ ሁለት ሴቶች ሁለቱን ኪዳኖች ይወክላሉ ሲል፤ አንደኛዋ ማለትም አጋር የሕግን ነገር ወይም የሲናን ተራራ የምትወክል ሲሆን፤ ሳራ ደግሞ እግዚአብሄር በገባው ተስፋ ቃል መሰረት ስለወለደችው የጸጋውን ኪዳን ትወክላለች ማለት ነው።
4. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሁለቱ ሴቶች ቀደም ሲል ይወክላሉ ተብሎ ከተነገረን ነገር ባሻገር ምሳሌነታቸው በምን ሊመሰል እንደሚችል ሲናገር፤ አንደኛዋ በአሁኑ ጊዜ ባለችው ኢየሩሳሌም ማለትም በህግ የሚታመኑ አይሁዶች የሚኖሩባት ስትሆን፤ ሁለተኛዋ ደግሞ ገና ልትመጣ ያለችው አዲሲቷን ኢየሩሳሌም ትወክላለች ነው የሚለን። ጳውሎስ ራሱን የነጻዋ ልጅ አድርጎ ሲናገር ያካተተው፤ በአዲሱ ኪዳን ውስጥ የገቡና በክርስቶስ የተሰራውን ሥራ የተቀበሉትን ሁሉ በመጨመር ነው።
5. በእኔ አመለካከት ይህ ቁጥር 27 ሊናገር የፈለገው ሃሳብ ከላይ ያነበብነውን የአጋርንና የሳራን ሁኔታ የሚገልጽ ይመስለኛል። በጊዜው አጋር ባለልጅና ወላድ ስትሆን፤ ሳራ ግን ለጊዜው ያለልጅ እንደነበረች ይታወቃል፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሄር ለአብርሃም በገባው ቃል መሰረት ከምድር አሸዋ የሚበዛ ዘር እንዳገኘች ሁሉ፤ ቤተ ክርስትያንም አጀማመሯ ትንሽ ቢሆን እንደምትሰፋና ምድርን እንደምትሞላ የሚነግረን እውነት ይመስለኛል።
6. በዘፍጥረት 21:8-10 ላይ እንደምናነበው የባርያይቱ ልጅ እስማኤል በነጻይቱ ልጅ በይስሃቅ ላይ ሲያሾፍና ሲያላግጥ እንደነበረና በዚያም ምክንያት ከአብርሃም ቤት እንደተባረረ ስለሚነግረን፤ አሳዳጁ እስማኤል ተሳዳጁ ደግሞ ይስሃቅ እንደሆነ እናያለን ማለት ነው። እስማኤል የአብርሃም ወራሽ እንደሆነ በማሰብ በይስሃቅ ላይ እንዳላገጠበት ሁሉ፤ አሁንም ቢሆን በሥራቸው የእግዚአብሄርን በረከት ለማግኘትና የእርሱን ተቀባይነት እንደሚያገኙ የሚመስላቸው ሰዎች በተስፋው ቃል መሰረት ክርስቶስን በእምነት ተቀብለው የሚኖሩትን እንደሚያላግጡባቸው እንደሚናገር ነው የማምነው።
7. ምንም እንኳን በአይሁድ ስርዓት ውርስ የሚሰጠው ማህጸንን ለከፈተ የበኩር ልጅ እንደሆነ ቢታወቅም፤ በዚህ ክፍል የተነገረን ግን ውርሱ በእድሜ ሳይሆን በአወላለድ ዓይነት ማለትም በተስፋ ቃል መሰረት ለተወለደው እንደሆነ ነው የምናየው።
8. የባርያይቱ ልጆች ወይም በራሳቸው ሥራ ወደ እግዚአብሄር ይደረሳል ብለው የሚያምኑ ሰዎች በዝተው መዘበቻ ሊያደርጉን ቢሞክሩም እንኳን፤ እኛ ነጻ የወጣን የነጻይቱ ልጆች እንደሆንና ውርሱም የእኛ እንጂ በእድሜ ታላቅነት የእስማኤል እንዳልሆነ በዚህ ክፍል ያነበብነው ክፍል ቁልጭ አድርጎ ስለሚናገር ትልቅ መጽናኛና ተስፋ ይሆነናል ብዬ አምናለሁ።

# ጥናት ዘጠኝ ገላትያ 5፡1፡12 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቁጥር ላይ “ዳግመኛም በባርነት ቀንበር አትጠመዱ” በማለት የሰፈረው ሃሳብ የሚጠቁመኝ ነገር ቢኖር፤ ከዚህ ቀደም በባርነት ቀንበር ውስጥ ተጠምደን እንደነበረ፤ ሆኖም በክርስቶስ በኩል ከዚህ ባርነት እንደተላቀቅንና ነጻ ሰው እንደሆንን ሲያሳየን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተመልሰን የነበርንበት ሁኔታ ውስጥ ተመልሶ መግባት እንደሚቻል የሚያስጠነቅቅ ሃሳብ ነው። ይህንን በክርስቶስ የተገኘውን ነጻነት ተግቶ መጠበቅ የእኛ ነጻነቱን የተቀበልነው ሰዎች ሃላፊነት እንደሆነ ነው የምናነበው።
2. የገላትያ አማኞችን በክርስቶስ ውስጥ ስላገኙት ነጻነት ከነገራቸው በኋላ ወዲያው ወደ ማስጠንቀቂያው በማለፍ የግርዛትን ሕግ ለመጠበቅ ዓላማና ሃሳቡ ላላቸው ሰዎች፤ በመገረዝ የእግዚአብሄርን ሕግ እንጠብቃለን ብላችሁ ካመናችሁ በመገረዝ ላይ ብቻ ማቆም አትችሉም፤ ምክንያቱም መገረዝ የሚፈልግ ሁሉ ሕግን በሙሉ የመፈጸም ግዴታ አለበት በማለት ነው የሚያስጠነቅቃቸው። ለእነዚህ አማኞች ጳውሎስ ሊል የፈለገው ነገር፤ ሕግ መገረዝ ብቻ ስላልሆነ ሕግን በመፈጸም የመዳን ሃሳብ ካላችሁ ለእናንተ የክርስቶስ መሞት ምንም ፋይዳ እንደሌለው ስለቆጠራችሁት ለእናንተ ምንም አይጠቅምም ነው የሚላቸው።
3. ማንኛውም ሰው አይሁዳዊም ሆነ ሌላ በክርስቶስ ከሚገኘው ነጻ የጽድቅ መንገድ ወጥቶ ሌላ ወደ እግዚአብሄር የመድረሻ መንገድ ማማቻቸት ከጀመረ፤ ጳውሎስ ሁለት ነገሮችን ይነግረናል፤ አንደኛው ከክርስቶስ ተለይታችኋል፤ ሲለን ሁለተኛው ደግሞ ከጸጋ ርቃችኋል በማለት አደገኛነቱን ያስገነዝበናል።
4. ጳውሎስ በቁ5ት ላይ የሰፈረውን ሃሳብ ሲናገር አማኞች ገና አልጸደቁም፤ ወይም ደግሞ ጽድቃችን ገና ወደፊት የምንጠብቀው ነገር ነው ማለቱ ሳይሆን፤ በ1ኛ ቆሮ 6፥11 ላይ “እናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል።” በማለት መጽደቃችንን በጳውሎስ አዕምሮ ጥያቄ ያለው ነገር እንዳልሆነ እናያለን፤ በዚህ ክፍል የሚናገረው ግን የእምነታችንና የጽድቃችን ማረፊያ የሆነውን ኢየሱስን ስለመጠበቅ የተናገረው እውነት እንደሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል።
5. ጳውሎስ ሁለቱን የአገልግሎት አጋሮቹን አንደኛውን ማለትም ቲቶን አለመግረዙና፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጢሞቲዎስን መግረዙ የሚነግነን ነገር ቢኖር፤ የጳውሎስ ትኩረት በመገረዝ ወይም ባለመገረዝ ላይ ሳይሆን የወንጌልን የምሥራች ለሰዎች ለማድረስ የሚጠቅመው ነገር የትኛው ነው የሚለውን መርሆ ሲከተል ነው የምናየው። ጳውሎስ መገረዝ ወይም አለመገረዝ ለደህንነት አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ቢያምን በሁለቱም አጋሮቹ ላይ ተመሳሳይ ነገርን ይፈጽም እንደነበረ አጠያያቂ አይሆንም።
6. ያዕቆብ በመልዕክቱ ውስጥ ማለትም እነዚህን ሁለት ጥቅሶችም ጨምሮ በመደጋገም እምነት አለኝ ለሚሉ ሰዎች እምነታቸውን በተግባር ማሳየት እንደሚጠበቅባቸው፤ ያ ካልሆነ ግን በሥራ የማይገለጽ እምነት ምውት እንደሆነ በማያወላዳ መንገድ አስፍሮታል። ጳውሎስም በዚህ ስፍራ የእምነትን ተግባራዊነት የሚናገር ሲሆን ከዚያም አልፎ ድርጊቱ ደግሞ በፍቅር የሚደረግ መሆን እንደሚኖርበት ስለሚናገር እነዚህ ሁለት ሰዎች ተመሳሳይ ሃሳብን እንደሚያስተምሩ መመልከት ይቻላል።
7. እነዚህን ሁለት ቁጥሮች ስናነብ በተለይም ቁ11 ላይ መስቀል እንደ እንቅፋት ሆኖ ሲነገር ነው የምናነበው። ይህም ማለት በተለይም በሕግ መዳንን ለሚያምኑት ሰዎች የክርስቶስ መስቀል ነገር ሞኝነትና ለማመን አስቸጋሪ እንደሆነ እንደሚሆንባቸው መጽሐፍ ቅዱሳችን ይነግረናል።
8. ሐዋርያው ለገላትያ አማኞች የሰጣቸው ማስጠንቀቂያ፤ በጊዜው ትንሽ መስሎ የሚታየው እርሾ ብዙውን ሊጥ ሊያቦካ እንደሚችልና ስለዚህም በቸልታ መመላለስ እንደማይኖርባቸው ነው ያስጠነቀቃቸው። አሁንም በዚህ ዘመን ለምንኖረው አማኞች ከእነርሱ የተለየ ነገር ስለማይጠበቅ ትንሽ የሚባል ነገር ሳይኖር ከሐጥያትን የምንችለውን ያህል ርቀት ጠብቀን መሄድ እንደሚኖርብን መማር እንችላለን።

# ጥናት አስር ገላትያ 5፡13-26 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጳውሎስ በቁ13 ላይ አማኞች ስለተጠሩበት ጥሪ የሚናገራቸው ሶስቱ እውነቶች፡- አንደኛው ይህ ጥሪ የነጻነት ጥሪ ነው ይለናል። ሁለተኛው እውነት ይህ ነጻነት ሥጋዊ ምኞታችንን ለመፈጸሚያ መጠቀም እንደማይገባን፤ ሶስተኛው እውነት ደግሞ ይህ ነጻነታችን ሌላውን ለማገልገል የምንጠቀምበት ነገር እንደሆነ ያስተምረናል። ስለተቀበልነው ነጻነት የተመለከትነው በተለይም ሶስተኛው እውነት "አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል" ሲል አንድ ሰው ለብቻው በራሱ ሊገላገልና ፍቅሩን ለቴሌቪዥን ሊገልጥ ስለማይችል፤ አማኝ በክርስቶስ የተቀበለውን ነጻነት ለመለማመድ ከሌላ አማኝ ጋራ መሆኑ የግድ እንደሆነ እንመለከታለን።
2. እኔ እነዚህን ሁለት ሃሳቦች ቅራኔ እንዳላቸው አድርጌ አላያቸውም ምክንያቱም፤ ቁ14 በቁ13 እና በቁ15 መሃል የሰፈረ ሃሳብ ሲሆን ዓውዱን ስንመለከት ጳውሎስ እየተናገረ ያለው አማኞች እርስ በእርሳቸው የሚኖራቸውን ግንኙነት አስመልክቶ በመሆኑ፤ እግዚአብሄርን የመውደዱን ነገር እዚህ ላይ መጥቀሱ አስፈላጊ ሆኖ ስላላገኘው ብቻ ነው እላለሁ።
3. አንደኛችን ሌላችንን በፍቅር ማገልገል ነጻ ከወጣንበት ምክንያት ዓላማ ጋራ የሚጣጣምና የሚስማማ ቢሆንም እንኳን፤ በዚህ እውነት ላይ በማመጽ ወንድማችንንና እህታችንን በፍቅር ከማገልገል ይልቅ መናከስንና መባላትን ምርጫችን ልናደርግ እንችላለን ማለት ነው። ይህንን ሁለተኛውን አማራጭ በመውሰድ ሕይወታችንን ለመምራት ስንወስን ግን ከቁ15 ላይ እንደምንረዳው እኛ ብቻ ሳንሆን ለሁላችንም የመጠፋፊያ መንገድ ሊሆንብን እንደሚችል ይነግረናል።
4. የሥጋችንን ምኞት አለመፈጸም እንዲሁ በሥጋችን ሃይል ማድረግ የሚቻል ነገር እንዳልሆነ ስለሚያውቅ፤ በቁ16 ላይ ይህንን ለማድረግ ከፈለግን በመንፈስ ቅዱስ ሃይል መመላለስ እንደሚኖርብን ያስተምረናል። (ዘካ 4፡6 እና ዮሐ 15፡5) ትንም በተጨማሪ ማየት ይረዳል።
5. የሰው ልጅ ምንም እንኳን አንድን ነገር ለማድረግ ፍላጎት ቢኖረውም ያንን የፈለገውን ለማድረግ እንደማይችል በመግለጽ ምክንያቱንም ጭምር ቁ17 ይነግረናል፤ መንፈስና ሥጋ ሁለቱ ተቃራኒ ፍላጎት ስላላቸው አንዱ ይህንን ሲለን ሌላው ደግሞ ያንን ስለሚለን ነው። አማኝ በራሱ ለማሸነፍ የሚያደርገውን ትግሉት በመተው ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ማስገዛት መለማመድ እንደሚኖርበት ነው እኔ ከዚህ ክፍል የምገነዘበው።
6. አማኝ በመንፈስ እየተመላለሰ እንደሆነ ወይም ደግሞ የሥጋውን ምኞት እየፈጸመ እንደሆነ የሚያውቅበት መንገድ፤ ሁለቱም ዓይነት አኗኗሮች የራሳቸው የሆነ ውጤት ወይም ፍሬ እንዳላቸው ሁሉ፤ ሰው የሥጋውን ምኞት እየፈጸመ ሲኖር በቁ19-21 ላይ ያሉት ነገሮች በሕይወቱ ግልጽ ሆነው የሚታዩ ሲሆን፤ በመንፈስ በሚመላለስ ሰው ላይ የሚታዩት ነገሮች ደግሞ በቁ22-23 ላይ የመንፈስ ፍሬ በመባል የተዘረዘሩት ነገሮች በሕይወቱ ግልጽ ሆነው መታየታቸው ነው።
7. ሰው ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋራ መስቀሉን በይፋ የሚያረጋግጥበት መንገድ ምን መሆኑን ለጥናቱ ካነበብነው ክፍል ግልጽ ሆኖ ይታያል ብዬ አምናለሁ፤ ይኸውም የዚያ ሰው ኑሮና አካሄዱ በቁ22-23 ላይ ሰፍረው የሚገኙትን ፍሬዎች በሕይወቱ ሰዎች ሊጠራጠሩ በማይችልበት መንገድ ተግባራዊ ሲያደርግ ያ ሰው ሥጋውን ሰቅሏል ማለት እንችላለን።

# ጥናት አሥራ አንድ ገላትያ 6፡1-10 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ከዚህ ቁጥር ለእኔ ቢያንስ አራት እውነቶች ይታዩኛል። የመጀመሪያው ክርስትያኖች በሃጥያት ውስጥ ሊገኙ እንደሚችሉ ፤ ሁለተኛው አማኞች በሃጥያት ውስጥ ሲገኙ ዝም ብሎ ማየት ተገቢ እንዳልሆነ፤ ሶስተኛው ደግሞ በሃጥያት የተገኙ ሰዎችን ለማቅናት መንፈሳዊያን ሰዎች እንደሚያስፈልጉና፤ አራተኛው ደግሞ መንፈሳዊያን ሰዎችም ቢሆኑ በሃጥያት ሊፈተኑ ስለሚችሉ መጠንቀቅ እንደሚኖርባቸው ማየት ይቻላል።
2. ሐዋርያው ጳውሎስ በሃጥያት የሳተውን ሰው የሚያቀናውና የሚመልሰው ሰው መንፈሳዊ የሆነ መሆን እንዳለበት የነገረን ሲሆን፤ ይህንን ድርጊት የሚያደርግ ማንኛውም ሰው ቢሆን ገርነት በተሞላበት መንፈስ (gently) ማድረግ እንደሚኖርበትም ጨምሮ ነግሮናል። ሊፈተንበት የሚችለው አንደኛው ነገር በልቡ እኔ ከዚህ ፈተና በላይ ነኝ ብሎ የማሰብ ነገር፤ ማለትም የትዕቢት አመለካከት ውስጥ ተዘፍቆ ከመገኘት እንዲጠነቀቅ ይመስላል። ለዚህ ይመስለኛል በገርነት ወይም በትህትና እንዲያደርግ የተነገረው።
3. በሌሎች ክፍሎች ውስጥ የምናገኘው በሙሴ አማካኝነት የተሰጠው ሕግ ሰዎችን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንጂ ያንን ሕግ ለመፈጸም የሚያስችላቸውን ምንም ዓይነት አቅም ወይም ጉልበት የማይሰጣቸው እንደሆነ ይታወቃል፤ በዚህ ክፍል የገላትያ ሰዎች እንዲፈጽሙት የተነገራቸው “የክርስቶስ ሕግ” በመባል የሚጠራው ሕግ ግን ሰዎች እንዲያደርጉት የሚያዝ ብቻ ሳይሆን ያንን ትዕዛዝ ወይም ሕግ ማድረግ የሚችሉበትንም ሃይል አብሮ የተሰጠ በመሆኑ በአድራጊው ላይ የወደቀ ሸክም እንዳልሆነ ሊታወቅ ያስፈልጋል።
4. ለእኔ እንደሚገባኝ ከሆነ ከላይ የተነገሩት ሁለት ቁጥሮች የወደቀን ሰው ከማንሳት ጋራ የተነገሩ ስለሆነና ይህም በትህትና መደረግ እንዳለበት የተነገረ ሲሆን፤ ሌላን ሰው መርዳት ከሌሎች የተሻሉ መሆን ማለት እንዳልሆነና ራሱን እንደተለየ ሰው አድርጎ በትዕቢት ማሰብ እንዳይጀምር በማስጠንቀቂያነት የተነገረ ነው።
5. በእነዚህ አምስት ቁጥሮች ውስጥ የምንመለከታቸው ሁለት ዓይነት ሸክሞች፤ የመጀመሪያው በቁ2 ላይ የምናገኘው ሌሎች ሊያግዙን የሚገባ የሸክም ዓይነት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በቁጥር አምስት ላይ የምናየው እኛ ራሳችን በግላችን ልንሸከመው የሚገባን ዓይነት ሸክም ነው። ቁ5 ላይ እንደምንመለከተው ከሆነ ሸክም የማይኖረው ምንም ሰው እንደሌለና ሰው ሁሉ የራሱ የሆነ ሸክም እንደሚኖረው እንረዳለን።
6. በዚህ ቁጥር ላይ ሐዋርያው በአስተማሪውና በሚማረው ሰው መሃል ሊኖር ስለሚገባው የግንኙነት የሚነግረን ነገር፤ መልካም የሆነውንና ሰማያዊውን የእግዚአብሄር ቃል ሲያካፍሉን፤ እኛ ደግሞ ማናቸውንም መልካም የሆነውን ለኑሮ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ከእነርሱ ጋራ መካፈል እንደሚጠበቅብን ነው የሚነግረን። እንቅፋቶች አሉ ብዬ አምናለሁ፤ ከእነዚህም መሃል ቃሉን የሚያስተምሩ ሰዎች ከሚናገሩት ቃል ጋራ የማይጣጣም ሕይወት መኖር ለብዙዎች ፈተና እንደሚሆን ይታወቃል፤ ሌላው ደግሞ ከቃሉ ይልቅ በራሳቸው ላይ ያተኮረ ነገር መስበካቸውም ሌላው ፈተና ሲሆን አገኝቼዋለሁ።
7. በመዝራትና በማጨድ መካከል የሚኖረው ቀጥተኛ ግንኙነት የሚከተለውን ይመስላል። ሰው ከዘራው ነገር የተለየ ውጤት መጠበቅ አይኖርበትም፤ ማለትም የዘራውን ያንኑ ነገር ነው የሚያጭደው፤ ይህ በሥጋዊው ዓለም ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊውም ዓለም ያንኑ መርሆ የተከተለ ነው።
8. ማንኛችውም አማኝ መልካም ሥራን መሥራት ትክክል እንደሆነ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ለማድረግም የሚሞክር ይመስለኛል፤ ሆኖም ሁለቱ ትልቅ ፈተና ሆነው የሚገኙት ነገሮች በገላ 6፡9 ላይ ሰፍረው የምናገኛቸው የመጀመሪያው መታከት ወይም መሰልቸት የሚባለው ሃሳብ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ተስፋ መቁረጥ የሚሉት ናቸው።
9. በማር 12፡29-31 ላይ ጌታ እንደተናገረው ሃሳብ ከሆነ አምላካችንን በሁለትንተናችን መውደድና፤ ሰዎችን ደግሞ እንደራሳችን መውደድ የእርሱን ሕግ እንደመፈጸም የሚቆጠር ከሆነ፤ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ሸክም ከብዷቸው ሲንገዳገዱ እያየን ዝም ማለት እንደ ክርስቶስ ደቀመዝሙር ትክክለኛ ነገር እንዳልሆነ ሲያስረዳን ይመስለኛል።

# ጥናት አሥራ ሁለት ገላትያ 6፡11-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ከዚህ ዛሬ ካነበብነው ምንባብ እንደምንመለከተው ሐዋርያው ሃሳቡን ያነጣጠረባቸው ሰዎች የገላትያን ክርስትያኖች መገረዝ ያስፈልጋቻኋል በማለት በጸጋ ያገኙትን አርነታቸውን ወደሕግ ሊመልሷቸው በሚጥሩት ሰዎች ላይ ነው። አማኞችን ወደ መገረዝ ወይም ወደሕግ ለመመለስ የሚሞክሩባቸው ሁለቱ ምክንያቶች፡- የመጀመሪያው ውጫዊ በሆነ ነገር ለመታየት ስለሚፈልጉ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ስለክርስቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ነው።
2. እኔ እንደምረዳው ከሆነ አንዱ ሰው በተገረዘው ሌላው ሰው መመካት የሚችለው፤ ልክ በዘመናችን ሰዎች በዚህም ሆነ በዚያ መንገድ ወደ ቤተክርስትያን መምጣታቸውና የቤተ ክርስትያን ወንበር በመሙላት ቁጥር መጨመሩ ለአንዳንድ ሰዎች የመጡት ሰዎች የህይወት ለውጥ ይኑራቸው አይኑራቸው ምንም ሳይገዳቸው መቀመጫ መሙላቱና ቁጥር የሰዎች ቁጥር መብዛቱ ብቻ የሚኩራሩበት ነገር እንደሆነ ሁሉ፤ እነዚህም ሰዎች የተገረዙ ደቀመዛሙርትን ቁጥር መጨመራቸው መኩራሪያ ይሆንላቸዋል ማለት ነው።
3. ጳውሎስ እነዚህ ሰዎች ራሳቸው ሕግን አይጠብቁም ሲል፤ በያዕ 2፥10 ላይ "ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል" እንደሚለው ሁሉ እነዚህ ሰዎች በሥጋ ይገረዙ እንጂ ሕግን ሁሉ ጠብቀዋል ማለት እንዳልሆነ ሲያስረዳ ነው።
4. ጳውሎስ "መገረዝም ሆነ አለመገረዝ አይጠቅምም" በማለት የተናገረው፤ በመገረዝም ሆነ ባለመገረዝ ከእግዚአብሄር ጋራ እርቅ ማድረግ አይቻልም፤ ወይም ደግሞ በእነዚህ ነገሮች አዲስ ፍጥረት መሆን አይገኝም ለማለት ሲሆን፤ ጢሞቲዎስን በሐዋርያት ሥራ ላይ የገዘው ደህንነት እንዲያገኝ ሳይሆን ለሌሎች የወንጌል እንቅፋት እንዳይሆን በማለት ነው። ከእግዚአብሄር ጋራ መንገድን ለማስተካከል የሚያስፈልገው አንዱና ወሳኙ ነገር በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆን እንደሆነ ጳውሎስ ግልጽ አድርጎ በቁ15 ላይ አስፍሮልናል።
5. በቁ16 ላይ ጳውሎስ ይህ ትዕዛዝ በማለት የሚናገርለት በቁ15 ላይ የተናገረውን ሃሳብ እንደሆነ አድርጌ ነው የምወስደው፤ ይኸውም በሕግ ማለትም በመገረዝ ወይም ባለመገረዝ ሳይሆን፤ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የመሆንን ሕግ በሚከተሉ ላይ የሚለውን ሃሳብ ነው።
6. በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ በሐዋርያው ጳውሎስና በሃሰት አስተማሪዎቹ መሃል የማየው ልዩነት ቢኖር፤ ሃሰተኞቹ አስተማሪዎች የሚመኩበት ውጫዊ በሆነና ስንት ሰዎችን ወደ መገረዝ በማምጣታቸው ሲሆን፤ ጳውሎስ ግን ትምክህቱ በክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል እንደሆነ ያለሁ።
7. ጳውሎስ ትምክህቱን በክርስቶስ መስቀል ላይ ማድረጉ ሌላ የሚመካበት ነገር ስላጣ አይደለም፤ ምክንያቱም በፊሊ ምዕራፍ ሶስት ውስጥ በተለይም በቁ3 እና በቁ4 ላይ መመካት አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝ እርሱ ከማንም የበለጠ ሊመካ የሚችልበት ነገር እንዳለው በመናገር፤ ወረድ ብሎ ደግሞ ዝርዝሩን አስፍሮታል። ማንም ሰው ሊመካ የሚፈልግ ከሆነ ያንን ለማድረግ ትክክለኛ ጊዜ እንዳለውና ያም ደግሞ ጌታችን በሚገለጠበት ጊዜ እንደሆነ ስለራሱ በመናገር ሃሳብ ይሰጠናል።
8. ጳውሎስ እኔ ለዓለም ተሰቅያለሁ በማለት በዚህ ሥፍራ ሲናገር፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት እኔም በእርሱ ውስጥ ሆኜ የሞትኩ ስለሆነ ከአሁን በኋላ ልክ ገላ 5፡24 ላይ "የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር ሰቅለውታል።" እንደሚለው ሁሉ ከዚህ ቀደም ከዓለም አገኛለሁ ብዬ የምሯሯጥላትን ደስታ፣ ሰላምና የመሳሰለውን ሁሉ ለማግኘት ዛሬ ምንጭ የሚሆነኝ ክርስቶስ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በውስጤ የነበረው ክፉ ምኞትና መሻት ደግሞ በጽድቅ ረሃብ ተሞልቷል ማለቱ ይመስለኛል።